# የኢትዮጵያ ወጣቶችና አገዛዝ

መስፍን ወልደ ማርያም

ሚያዝያ 1996

ዋሺንግተን ዲ.ሲ.

## 1. ወጣትነት

መጀመሪያ ወጣት ምን ማለት ነው? ወጣትነት ያለቀና ያበቃ ሁኔታ አይደለም። ወጣትነት በሕይወት ውስጥ አጭር ጉዞ ነው፤ የሚያልቅ ጉዞ ነው። ወጣት ማለት በማደግ ላይ ያለ ሰው ነው፤ ማደግ የማያቆም ቢሆንም ወጣት መሆን መጨረሻ አለው። ይህ በማደግ ላይ ያለ ወጣትነት መጀመሪያ አለው፤ መጨረሻም አለው። ምናልባት የወጣትነት መጀመሪያው የልጅነት መጨረሻው ይሆናል፤ ምናልባትም የወጣትነት መጨረሻው የሽምግልና መጀመሪያ ይሆናል። ቁምነገሩ ያለው በወጣትነትና በሽምግልና መሀከል ባለው ዘመን ሙሉ ሰው መሆን ላይ ነው። ስለዚህም ወጣትነት ለሙሉ ሰውነት ዝግጅት ነው ለማለት እንችላለን። ሙል ሰውነት ደረጃ ላይ መድረሳችን የሚታወቀው በችሎታችንና በማነበረሰባችን ውስጥ ባለን አቋም ነው፤ ማኅበረሰባችን የምለው አውቄ ነው፤ ምክንያቱም ከሕፃንነት ውልጅነት፣ ከልጅነት ወደወጣትነት፣ ከዚያም ወደ ሙሉ ሰወነትና ወደሽምግልና የምንተላለፍበት ደረጃ የተያያዘና የተሰካካ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ችሎታ የሚገኘው በትምህርትና በመመራመር ነው። ማሰብ፣ መማርና መመራመር የእውቀት ባለሥልጣን ያደርጋል። ወጣቶች የአገር ሀብትና አለኝታ የሚሆኑት የእውቀት ባለሥልጣን ሲሆኑ ነው። የእውቀት ሥልጣን የሚገኘው ከዩኒቨርሲቲ ነው፤ ከሁሉ በፊት ዩኒቨርሲቲ መካነ ነጻነት ነው፤ ነጻነት የሌለበት ዩኒቨርሲቲ ሞተሩ እንደወለቀ መኪና ነው፤ ተግባሩን ስለተወ ዋጋ የለውም። ዩኒቨርሲቲ መካነ ጽድቅና (እውነት) መካነ እውቀት ነው። እውነትና እውቀት አይለያዩም፤ ዩኒቨርሲቲ የወጣቶች አእምሮ በሰውነትና በሕገ ኅልዮት የሚገራበትና የሚሠለጥንበት ደብር ነው። በዚህ ደብር ውስጥ የሚማሩ ወጣቶች ከሰውነት ደረጃ ወርደው በዘርና በጎሣ ጎራ ሲለዩ የዩኒቨርሲቲን ባሕርይ ስላልተገነዘቡ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ዩኒቨርሲቲውንም ያረክሱታል።

ወጣቶች የመማር፣ የማሰብና የመመራመር መብትን አግኝተው በእውቀት ሲካኑ እውቀታቸው ወደሥልጣን ይለወጣል፤ ወያኔ ይህንን እንደማይፈልግ በተለያየ መንገድ አሳይቶአል፤ እንዲያውም የመጀመሪያ ዓላማው አድርጎ የራሱን የወያኔን የአለማወቅ ጉድፍ ወደዩኒቨርሲቲ መምህራን ለማስተላለፍ ሳያፍር ሞክሮ ነበር። እስከዚህ ድረስ የደነደነ ድንቁርና ነው ያለው። ሳይሆንለት ሲቀር መምህራኑን ጠራርጎ አስወጣቸው፤ ችሎታ የሌላቸውም ብሎ ሲጽፍላቸውም አላፈረም። ዩኒቨርሲቲውን አዘቅት ውስጥ በመክተት የአገሪቱን የእውቀት እርምጃ ቢያንስ ሠላሳ ዓመታት ወደኋላ መልሶ፣ የአገሪቱን እንጋፋ ዩኒቨርሲቲ የሰዎችና የእውቀት ሳይሆን የጎሣዎች መናኸሪያ አደረገው። ዛሬም ድረስ ስሙን ተሸክሞ ባዶ ነው። ደርግም ወደዚህ ደረጃ አላወረደውም ነበር። በወንበሩ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ወያኔ ከትምህርትና ከእውቀት ጋር ያለውን ጠብ በማያሻማ ሁኔታ አሳይቶአል።

በቅርቡ እንደገና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታየው የኦሮሞ ተማሪዎች እንቅስቃሴና በመቀጣጠል ላይ ያለው ውጤቱ በአንድ በኩል የተዘራው በማበብ ላይ መሆኑን ሲያመለክት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የማናለብኝነቱ ደረጃ የት እንደደረሰ ያሳያል። ለአን

ድ ዓመት ከዩኒቨርሲቲ በጅምላ የተባበረሩት የኦሮሞ ተማሪዎች በአንድ በኩል ሁሉም
ኦሮሞዎች መሆናቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎቹ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ በማቅ
ረባቸው ብቻ መባረራቸው ችግሩ ሌላ መልክን እንዲይዝ አድርጎአል። በመላ ኦሮች
ሚያ ትምህርት ቤቶች ወይ ተዘግተዋል፤ ወይም የተረበሸ ሁኔታ ውስጥ ናቸው። ቀደ
ም ሲል በአዋሳ፣ በቴፒ፣ በቅርቡ ደግሞ በጋምቤላ የተፈጸመው ጭፍጨፋ ወያኔ ከተ
ለያ ዩጎዝዎች ጋር ያለው ቅራኔ እያሰፋ በመሄድ ላይ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።
ይህ አዲስ ሁኔታ አገሪቱን ወደሌላ ውስብስብ ችግር ውስጥ እንዳይከትታት ያሰጋል።

የእውቀት ባለሥልጣን ለመሆን በሚያደርጉት ጥረት ሁሉ ሙሉ የማሰብና ሀሳባ
ቸውን በተፈለገው መንገድ የመግለጽ ነጻነት ያስፈልጋቸዋል፤ አእምሮ በጉልበት አይመ
ራም፤ ጉልበት የሕገ አራዊት ነው፤ አእምሮ የሚመራው በሕገ ኅልዮት ነው። ወጣቶች
ሲማሩና ሲመራመሩ ስለማኅበረሰባቸውም ሆነ ስለዓለም በአጠቃላይ ብዙ ጥያቄዎችን
ያነሳሉ፤ አማራጭ አስተያየቶችን ያቀርባሉ። እንግዲህ ወደሙሉ ሰውነት ለመሸጋገር
የሚፈልጉ ወጣቶች ማሰብ ይፈልጋሉ፤ መማር ይፈልጋሉ፤ ለማሰብም ለመማርም መጠ
የቅ፣ ማናቸውንም ነገር መጠየቅ ይፈልጋሉ።

በሌላ በኩል ሲታይ ደግሞ የቀረውና ከነሱ ዕድሜ በላይ ያለው ቁልቁለቱን በ
መውረድ ላይ ሲሆን ወጣቶች ዳገቱን እየወጡ ናቸው። ይህ የመውጣትና የመውረድ
ጉዞ የተፈጥሮ ሕግን ጠብቆ የሚፈጸም ይሆናል፤ ዳገቱን የወጡት ቁልቁለቱን ሲፈሩት
ና ዳገቱን በመውጣት ላይ ያሉት ደግሞ ናዳውን ሲፈሩት ማኅበረሰቡ መንቀሳቀስ ያቆ
መና ሕያውነቱን ያጣ ይሆናል፤ ለአንድ ማኅበረሰብ የእድገት እንቅስቃሴ የሆነው የት
ውልዶች ቅብብሎሽ አቀባዩንም ተቀባዩንም በያዛቸው የፍርሃት ቆፈን ደርቆ ይቆማል።
በአሁኑ ጊዜ በሁለቱም በኩል የሚታየው ፍርሃትና ሽሽት ይህንን ሁኔታ የሚያንፀባርቅ
ነው። የሁለቱም ወገኖች ፍርሃትና ሽሽት የኢትዮጵያን የነጻነት ችግር አይፈታም፤ በተ
ናጠል እያንዳንዱ ወጣት ወይም የወያኔ ሹም ራሱን ከኢትዮጵያ ውስጥ ካለው አስከፊ
ሁኔታ ለማውጣት የሚያደርገው ሽሽት አይሳካም፤ ምክንያቱም ችግሩ ያለው በነፍሱ
ውስጥ ነውና ሲሸሽም ይዞት ይሄዳል። ከውስጥ እንደታፈኑ አፍአዊ አፋኙን ብቻ በመ
ሸሽ ነጻነት በጭራሽ አይገኝም፤ የአፋኙ ግዙፍና ጠንካራ ህልውና ምንጊዜም በታፋኙ
ነፍስ ውስጥ አለ፤ የሽሽቱ ምክንያት ነውና። አንዱና ትልቁ ችግራችን ፍርሃታችንን
ማሸነፍ አለመቻላችን ነው።

## አገዛዝና ወጣቶች

የመብት ጥያቄ ሰው የመሆን ጥያቄ ነው፤ ሰው የመሆን ጥያቄ ሁለት ዋና ነጥቦ
ች አሉት፤ አንደኛ፣ እያንዳንዱ ሰው ራሱ ሰው መሆኑን ተገንዝቦ በሚኖርበት ማኅበረ
ሰብ ውስጥ ያለውን መብትና ግዴታ ማወቅ አለበት። ሁለተኛ፣ ግፍን፣ በደልን፣ ጥቃ
ትን፣ አድልዎንና ሕገወጥነትን አልቀበልም፣ እምቢ የማለት ጠንካራ አቅዋም እንዲኖረ
ው ያስፈልጋል። የማሰብና ሀሳብን ከሌሎች ሰዎች ጋር የመካፈል መብት ሰው ከመሆ
ን የሚመነጭ ነው። ማሰብ የእያንዳንዱ ሰው የግል ተግባር ነው፤ በአንድ ሰው አእም
ሮ ውስጥ የሚካሄድ ሙግት ወይም ክርክር ነው። በአእምሮ ውስጥ ስለሆነ ማንም አያ
የውም፤ ማንም አይሰማውም፤ ማንም ሊያግደው አይችልም። ማሰብ የግል ተግባር የሆ
ነውን ያህል ሀሳብን መግለጽ ደግሞ ማኅበራዊ ነው። ሀሳብ ተገልጦ ካልወጣና ካልተፈተ
ሸ ጥቅሙና ጉዳቱ አይታወቅም። ስለዚህም መብሰልና መሻሻል፣ ማደግና መለወጥ የ
ሚገኘው በማሰብ ብቻ ሳይሆን ሀሳብን በመግለጽ አስተሳሰብን በመፈተሽና በማቃናት፣
በማበጠርና በማጥራት ነው። ችግርም የማያጋጥመው በማሰብ ላይ ሳይሆን ሀሳብን በ
መግለጽ ላይ ነው።

ሀሳብን መግለጽ ችግር የሚፈጥረው ለምንድን ነው? ማሰብ የኃይል ምንጭ፣ ሀሳብ ደግሞ ኃይል ነው። እያንዳንዱ ሰው በማሰብ ችሎታው መጠን ኃይል ይኖረዋል፤ ለዚህ ነው ፈረንጆች እውቀት ኃይል ነው የሚሉት። በማሰብ፣ በማንበብና በማዳመጥ የሚገኘው የእያንዳንዱ ሰው እውቀት ማኅበረሰቡንና አካባቢውን እየለወጠ ልማትን፣ እድገትንና መሻሻልን ያመጣል። በእኛ አገር የፈረንጆቹን አባባል አዙረን ሥልጣን ወይም ኃይል እውቀት እየሆነ ነው፤ እውቀት በብዙ ልፋት ሳይሆን በተቀመጡበት የሥልጣን ወንበር የሚገኝ ይመስላቸዋል። አላዋቂነታቸው በየቀኑ እያፈጠጠባቸው ገዢዎቻችንን የእውቀት ጠላቶች አድርጎአቸዋል፤ አምባገነኖች ማሰብና አዋቂ መሆን የለውጥ ኃይል መሆኑን ያውቃሉ፤ የለውጥ ኃይል መሆን ደግሞ ያለውንና ተሸፋፍኖ በድንቁርና ላይ የተመሠረተውን ሥልጣን እንደሚያነቃንቅባቸው ያውቃሉ፤ ማሰብንና ማወቅን ተቃውሞ የሚገጥመው እዚህ ላይ ነው። ቀደም ሲል በነበረው ባህላዊ አገዛዝ መለኮታዊ ሥልጣን አይጠየቅም ነበር፤ በዘመናዊ አገዛዝም ሌኒናዊ ፍልስፍና አይጠየቅም ነበር፤ የዛሬውም ግራ የገባው ጎሠኛ የጠመንጃ አገዛዝ ጥያቄን ይፈራል።

የመብት ጥያቄ የባለቤትነት ጥያቄ ነው፤ በልበ ሙሉነት የኔ አገር፣ የኔ ወገን፣ የኔ መንግሥት ብሎ ለመናገርና አብሮ ለመቆም የሚያስችል ሁኔታ መኖር አለበት። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ይህንን ለማለት የሚያስችል አይደለም፤ በጎሣ ተከታትፈናል፤ በዚያ ላይ ጥቂቶቹን ብቻ ለመጥቀስ ያህል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የውጭ ጉዳይ፣ የማስታወቂያ፣ የፌዴራል ጉዳይ፣ የአገር ውስጥ ገቢ፣ ሚኒስትሮች በሙሉ የአንድ ጎሣ አባሎች፣ የፖሊስና የጦር ኃይሉ አዛዦች ከዚያው ከአንድ ጎሣ ሲሆኑ፣ አዲስ አበባም በዚያው ጎሣ አባል ቁጥጥር ውስጥ ነው፤ ከዚህ እውነት ተነሥተን የሌሎች ጎሣዎች አባሎች የአገር ባለቤትነት ተሸሮአል ለማለት እንችል ይሆናል። ነገር ግን ከዚያው እውነት ተነሥተን የሌሎችን ባለቤትነት የሻሩት ትግሬዎች ናቸው ለማለት አንችልም። እንዲህ ያለ የተዛባ አስተሳሰብ የወያኔን ስሕተትም ይሁን ክፋት ማራባት ይሆናል። በሁለቱም በኩል ያለው የተዛባ አስተሳሰብ አባይና (ውሸታም) ስንቅ እያደር ይቀልላል እንደሚባለው እውነቱ ሲጋፈጣቸው ገለባ ይሆናሉ። የባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ የባለቤትነት መብትን የገፈፈውን በትክክል ለይቶ ማወቅን ይጠይቃል። የራስን ባለቤትነት ለማረጋገጥ የሌላውን ባለቤትነት መንፈግ ችግሩን ያሰፋዋል እንጂ አይፈታውም።

የመብት ጥያቄ የሥልጣን ጥያቄ ነው፤ የመማር፣ የማሰብ፣ የመመራመር፣ የእውነትን ፈለግ የመከተል፣ የማደግና የመሻሻል፣ በመጨረሻም ኃላፊነትን የመቀበል ጥያቄ ነው። የመብት ጥያቄ ድንቁርናን ወደእውቀት፣ ደህነትን ወደብልጽግና፣ ፍርሃትን ወደወኔ፣ ድካምን ወደጥንካሬ የመለወጫው መንገድ ነው። አገዛዝ ደግሞ ምንም ተጠያቂነትና ኃላፊነት ሳይኖርበት፣ ምንም ዓይነት ተቀናቃኝ ሳይገጥመው በጠመንጃ በማስፈራራት ብቻ ሕዝቡን በደህነትና በችጋር አዳክሞ እንደፈለገ ለመግዛት የሚመኝ ነው። ወጣቶችና አገዛዝ የባሕርይ ልዩነት አላቸው፤ ወጣት ከጊዜ ወደጊዜ የሚያድግና የሚለወጥ ነው፤ አገዛዝ የያዘውን ይዞ ሳይለወጥ ለመቆየት በጠመንጃ የሚጠቀም ቁሞ-ቀር ነው። ወጣቶች የተስፋ ተራራ በዓይነ አእምሮአቸው እያዩ ያንን ለመውጣትና የራሳቸውንም ሆነ የማኅበረሰቡን ኑሮ ወደተሻለ ሁኔታ ለመለወጥ የሚጥሩ ናቸው፤ አገዛዝ የተስፋ ተራራ የለውም፤ በአንፃሩ አገዛዝ የሚያየው የስጋት ቁልቁለት ብቻ ነው።

ወጣቱ በመማርና በማወቅ የአገሩ ባለቤት መሆኑን ሲገነዘብ በአገዛዙ ጭፍን አመራርና በወጣቱ የማሰብ ችሎታ መሀከል ክፉ ቅራኔ ይከሰታል። ወጣቶች የአገሩ ባለቤት መሆናቸውን ሲገነዘቡና ቆራጥ አቋም ሲይዙ አገዛዙን ስጋት ላይ ይጥለዋል። ይህንን በደንብ ለማስረዳት አንድ ታሪክ ልንገራችሁ።

የዛሬ ሃምሳ አምስት ዓመት ግድም በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ውስጥ ታይ
ቶ የማይታወቅ አድማ ተደርጎ ነበር፤ አጀማመሩ እንዲህ ነው፤ ጥቂት ተማሪዎች እት
ድ ለእረፍት ሄደው ሲመለሱ ያረፍዳሉ፤ ሰኞ ቀኑን ሙሉ እነዚህ ልጆች በዲሬክተሩ
በር ላይ ተቀምጠው በመዋላቸውና አንድ የትምህርት ቀን እንዲያልፍባቸው በመደረጉ
ተማሪ ተናደደ፤ ይህንን የተማሪ ንዴት የሰማ አንድ የታሪክ አስተማሪ ተቆጥቶ ክፍል
ውስጥ 'አያቶቻችሁም አባቶቻችሁም በጫካ ሲኖሩ የነበሩ ናቸው፤ እናንተም በጫካ
ብትኖሩ ይሻላችኋል፤' የሚል ነገር ይናገራል። ተማሪዎቹ ከክፍል ሲወጡ አንዳንዶቹ
ያለቅሱ ነበር። ወሬው ያንኑ ማታ በራት ላይ ተዛመተ፤ ምስካየ ሕዙናን መድኃኔ ዓለ
ም ሄደን ተማማልን። በበነጋታው ትምህርት አቆምን፤ ጠዋት የትምህርት ሚኒስቴር ዋ
ና ዲሬክተር መጡ፤ ተማሪ አልተበገረም፤ በምሳ ጊዜ ሚኒስትሩ መጡ፤ የተማሪው አ
ቅዋም እኛ የምንፈልገው ጃንሆይን ነው፤ የጻፍነውንም ደብዳቤ የምንሰጠው ለሳቸው
ብቻ ነው፤ ከዚህ ንቅንቅ አንልም አልን። በአሥር ሰዓት ጄኔራል መኮንን ደነቀ መጡ
ና ተሰበሰብን፤ የጃንሆይ ትእዛዝ ነው ብለው አሁኑኑ ትምህርታችሁን እንድትጀምሩ ተ
ባልን፤ የጃንሆይን ትእዛዝ ለመፈጸም ክፍል እንገባለን፤ ነገር ግን አስተማሪዎቹም አያስ
ተምሩንም እኛም አንማርም የሚል መልስ ሰጠን። በአሥራ ሁለት ሰዓት ጃንሆይ ከነል
ጆቻቸውና ከነሚኒስተሮቻቸው መጡ። በዚያን ጊዜ የታየው ቲያትር ሰፊ ነውና ወደዝ
ርዝሩ አልገባም፤ የተማሪዎቹን ቁርጠኛነት የሚገልጹ ሁለት ምሳሌዎችን ብቻ እጠቅሳ
ለሁ። አንዱ ጃንሆይ የተጻፈው ሲነበብ 'ከእግዚአብሔርና ከተማሪዎች በቀር የሚያው
ቀው የለም፤' የሚል ሲሰሙ ተናደዱና 'እኛስ! አናውቀውም?' አሉ፤ ድረስልኝ መስፍን
የሚባል ተማሪ በጥሩ ጎንደርኛ 'ጃንሆይ! ያየነውን የሰማነውን እንናገራለን፤' አላቸው።
በሌላ ሁኔታ ደግሞ ተናደዱና 'ከየተም ለቃቅመን አምጥተን' ሲሉ ማቴዎስ ጥግነህ የ
ሚባል ተማሪ 'ጃንሆይ! አባቶቻችን ታክስ ይከፍላሉኮ!' አላቸው። ብዙዎቻችሁ የጊዜ
ውን ሁኔታና የጃንሆይን ወደአምላክነት መጠጋት ለማታውቁ ታሪኩ እምብዛም አያስደ
ንቃችሁም፤ በጊዜው ግን ታይቶ የማይታወቅና ብዙ ሰዎች የኮሩበት ነበር።

ተማሪዎች ለአገራቸውና ለወገናቸው ተቆርቁረው ከተፈራና ከተከበረ መለኮታዊ
ሥልጣን ጋር ሲጋፈጡ አልፈሩም፤ የጃንሆይ አገዛዝም በአንድም ተማሪ ላይ አካላዊ
ጉዳት አላደረሰም። በዚህ ታሪክ ለማስረዳት የፈለግሁት ተማሪዎች፣ የከፍተኛ ትምህር
ትም ላይ ባይደርሱም የአገራቸውና የታሪካቸው ባለቤት መሆናቸው ሲሰማቸው የሚያ
ድርባቸው የመቆርቆር ስሜት ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ነው። ሁለተኛ፣ ለእመኑበት
እውነት በቆራጥነት መቆም መንፈሳዊ ወኔንና ድፍረትን ይሰጣል።

*መደምደሚያ*

ለመብት ለመታገል የራሳችን ብቻ ሳይሆን የማንም የሌላ ሰው ስቃይና መከራ፣
ግፍና በደል እንዲጋባብንና እስከነፍሳችን ጠልቆ እንዲሰማን ያስፈልጋል፤ ስሜታችን እ
ንዲህ መሆኑንና አለመሆኑን የምናውቀው እያንዳንዳችን ነን።